የቢጫ ወባ በሽታ

1. የበሽታው ምንነት እና ሥርጭት

የቢጫ ወባ በሽታ በድንገት በመነሣት ከፍተኛ ትኩሣት፣ ራስ ምታት፣ የጡንቻና የመገጣጠሚያ አካላት ህመም፣ ማቅለሽለሽና ትውኪያ የሚያስከትል ብሎም እየፀና ሲሄድ የሆድ ህመም ፣ ከአፍ ፣ ከአፍንጫ ፣ ከአይንና ከሆድ ዕቃ መድማት፣ እንዲሁም ደም በማስታወክና አይንን ቢጫ በማድረግ ለህልፈተ ህይወት የሚዳርግ በትንኝ ንክሻ አማካኝነት የሚተላለፍ በሽታ ነው። በበሽታው የተጠቁ ሠዎች አፋጣኝ ህክምና ካልተደረገላቸዉ እስከ 50 በመቶ የሚሆኑት ለእልፈተህይወት ይዳረጋሉ።

ወባ የሚለው ቅጥያ ስም በሃገራችን በተለምዶ የተሰጠው ወባ መሰል የህመም ምልክት ስለሚያሳይና ከባድ የወባ በሽታን ለመጠቆም ሲሆን ይህ ቢጫ ወባ በሽታ ከወባ በሽታ ጋር ምንም ግንኙት የለውም።

በሽታው በአፍሪካና በላቲን አሜሪካ በ44 ሃገሮች እንደሚገኝና በእነዚህ ሃገሮችም ውስጥ የሚገኙ ወደ 900 ሚሊዮን የሚገመቱ ህዝቦች ተጋላጭ እንደሆኑ የሚታወቅ ሲሆን ከዚህም በአፍሪካ 31 ሃገሮች ውስጥ 508 ሚሊዮን ህዝቦች ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ይኖራሉ። በሽታው በዓመት በመላው አለም እስከ 200,000 ህመምና እስከ 30,000 ሞት የሚያደርስ ሲሆን፣ በሃገራችንም ውስጥ በአንዳንድ ቦታዎች እንደሚገኝ ይገመታል።

7. ሪፖርት አደራረግ

1. ማንኛውም ሰው አጣዳፊ ትኩሳት ካለበት ና በአስራ አራት ቀናት ውስጥ አይኑ ቢጫ ከሆነ የቢጫ ወባ ታማሚ ነው ተብሎ ሊጠረጠር ይችላል። በሽታዉም በላቦራቶሪ ተመርምሮ መረጋገጥ ይኖርበታል።

2. አንድ ታማሚ በቢጫ ወባ በሽታ መታመሙ በላቦራቶሪ ከተረጋገጠ በሽተኛዉ ባለበት አካባቢ ወረርሽኝ መከሰቱን ይጠቁማል። በመሆኑም ጉዳዩን ለሚመለከታቸዉ አካላት በአስቸኳይ ማሳወቅ ያስፈልጋል። ከላይ እንደተጠቀሰው ማንኛውም ሰው ድንገተኛ የሆነና ከፍተኛ ትኩሳት ካለበት አይኑ ቢጫ ሆነም አልሆነም በአፋጣኝ ወደ ጤና ድርጅት እንዲሄድ በማድረግ በአካባቢ ላለ ጤና ድርጅትም ሆነ መንግስታዊ መዋቅር ሪፖርት ማድረግ ይጠበቅበታል። ከዚህ በተጨማሪ ማንኛውም የሞት ሁኔታ (ከአደጋ በስተቀር) በአካባቢያችን ካለ ወይም መኖሩ ከታወቀ በአቅራቢያዉ ለሚገኝ ጤና ድርጅት ሪፖርት ማድረግ ያስፈልጋል።

8. ጠቃሚ ምክሮች

1. **አካባቢን ለትንኝ መራቢያ ምቹ እንዳይሆን ማድረግ**
   - ውሃን ማቆር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ከአካባቢ ማስወገድ (የተጣለ ቆርቆሮ፣ጎማ፣ እንጨት .....)
   - ያቆሩ ውሐ ማአካላትን ማፍሰስና መድፈን
   - በማይደፈኑ ውሃማ አካባቢዎች የአቤት ኬሚካል /ቴሞፎስ/ በመጠቀም ትንኝ እንዳይራባ ማድረግ

2. **ቤትን በፀረ-ትንኝ ኬሚካል ማስረጨትና ግድግዳውን በእበት አለመለቅለቅ እና ሌሎች ነገሮች አለመቀባት**

3. **ክትባትን በአግባቡ መውሰድ**

4. **የህመም ስሜት ሲሰማዎ ፈጥነው ወደ ጤና ድርጅት በመሄድ ባለሙያ ማማከር**

5. **የታመመ ወይም የሞተ ሰው ሲኖር በቶሎ ለጤና ባለሙያዎች ሪፖርት ማድረግ**

ማንኛውም ከፍተኛ ትኩሳት እና የዓይን ቢጫ መሆን ምልክት ያለበት ስው በቢጫ ወባ የተያዘ ሊሆን ሥለሚችል በሽተኛን ወደ ጤና ድርጅት ይውሰዱ፤ በአቅራቢያ ላለ ጤና ጽ/ቤት ወይም የአስተዳደር አካላት በፍጥነት ያሳውቁ።

ስተጨማሪ መረጃ በሚከተሉት ይጠቀሙ፡-

የህብረተሰብ ጤና አደጋ ቁጥጥር ማዕከል፡-
Tel: +251 11 275 8631 OR +251 11 276 5340
Fax: +251 11 275 8634
Email: PHEMcenter@ehnri.gov.et Website: http://www.ehnri.gov.et

Ministry of Health | World Health Organization | unicef

2. መንስኤው እና የመተላለፊያ መንገዶች

የቢጫ ወባ በሽታ መንስኤዎች በትንኝ ንክሻ የሚተላለፍ በአይን የማይታዩ ረቂቅ ተህዋስያን ሲሆኑ እነዚህም የቢጫ ወባ ቫይረስ /አርቦቫይረስ/ ይባላሉ፡፡ የበሽታው አስተላላፊ ትንኝም እንደ ማንኛውም የወባ ትንኝ ዝርያ ሲሆን ቫይረሱን ከሰው ወደ ሰው፣ ከእንሰሳት /ጦጣ እና ዝንጀሮ/ ወደ እንሰሳት /ጦጣ እና ዝንጀሮ/ ወይም ከጦጣና ዝንጀሮ ወደ ሰው በማስተላለፍ በሽታዉ በወረርሽኝ መልክ እንዲከሰት ወሣኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ይህ የወባ ትንኝ በአብዛኛው በቀን ወቅት የሚነድፍና በሽታውን የሚያስተላልፍ እንደሆነ ይታወቃል፡፡

በአጠቃላይ በሽታው 3 አይነት የመተላለፊያ ኡደት አለው፡-

1. የጫካ አይነት ቢጫ ወባ - ይህ አይነቱ ቢጫ ወባ በበሽታው ከተያዙ ዝንጀሮዎች ወደ ሌሎች ዝንጀሮዎች በትንኝ ንክሻ የሚተላለፍ ሲሆን ከእነዚህ እንሰሳትም ወደ ጫካ ውስጥ ገብተው የሚሰሩ ሰዎች በትንኝ ንክሻ ሲተላለፍ ያለውን ኡደት ለማሣየት ነው፡፡ ይህም በተለይ በጥቅጥቅ ደኖችና ጫካዎች ውስጥ በሚሰሩ ሰዎች ላይ የሚከሰት ነው፡፡

2. ኢንተርሚዴት ቢጫ ወባ- /በጫካና በቤት አካባቢ / ዙሪያ / በሚራቡ ትንኞች የሚተላለፈው ቢጫ ወባ ሲሆን፣ ትንኞቹ በመኖሪያ አካባቢ እና በጫካ አካባቢ በመራባታቸው ምክንያት በሽታው በሰዎችና በዝንጀሮዎች መካከል እንዲዘዋወር ያደርጋሉ፡፡ የዚህ አይነቱ ቢጫ ወባ በአፍሪካ ውስጥ በተለይም ቤቶች ፈንጠር ፈንጠር ብለው በጫካ እና ጫካ አካባቢ በተሠሩባቸው አካባቢዎች ወረርሽኝ በማስነሳት ይታወቃል፡፡

3. የከተማ አካባቢ ቢጫ ወባ- የዚህ አይነቱ ቢጫ ወባ እንደ ከተማ ባሉና ህዝብ በብዛት በሚገኝባቸው አካባቢዎች ኤደስ ሞስኪቶ የተባለው የትንኝ አይነት በብዛት በሚገኝባቸው አካባቢዎች በሽታው ሲከሰት የሚያመላክት ሲሆን ይህም ያልተከተበና ለበሽታ ተጋልጦ የማያውቅ ህዝብ ውስጥ ሲከሰት ከፍተኛ ወረርሽኝ ሊያስነሣ ይችላል፡፡

3. አጋላጭሁኔታዎች

- በሽታውን አስተላላፊ ትንኝ በአካባቢው መኖሩ
- ለትንኝ መራቢያ ምቹ የሆኑ አካባቢያዊ ሁኔታዎች
- በአካባቢው የበሽታ መከሰት
- ክትባት አለመውሰድ

4. የቢጫ ወባ በሽታ ዋና ዋና ምልክቶች

አንድ ሰው በበሽታው በተያዘ ከ3-6 ቀናት ውስጥ የህመም ስሜቶችና ምልክቶችን ማሣየት ይጀምራል፡፡ ምልክቶቹም በ2 እርከን ሊከሰቱ የሚችሉ ሲሆን እስከ 85 በመቶ የሚሆኑ ሰዎች የመጀመሪያው እርከን ውስጥ ገብተው ከ3-4 ቀናት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ይሻላቸዋል፡፡ ነገር ግን 15 በመቶ ያህል በሚሆኑት ህሙማን ላይ የህመም ስሜቶች ቀንሰዉ፣ የመዳን ምልክት ካሳዩ በኋላ በ 24 ሰዓት ዉስጥ ወደ ሁለተኛውና አደገኛው እርከን በመግባት ተገቢውን የህክምና ዕርዳታ ካላገኙ እስከ 50 በመቶው ለህልፈተ ህይወት ይዳረጋሉ፡፡

በቢጫ ወባ በሽታ የተያዘ ሰው የሚከተሉት ዋና ዋና ምልክቶችና የህመም ስሜቶች ይኖሩታል፡-

በመጀመሪያው ደረጃ /እርከን /Acute phase/፡-
- ከፍተኛ ትኩሣት፣ ብርድ ብርድ ማለትና ማንቀጥቀጥ
- የጡንቻና የመገጣጠሚያ ቁርጥማትና ህመም
  በተለይም የወገብ ህመም
- ራስምታት
- የምግብ ፍላጎት መቀነስ /ማጣት
- ማቅለሽለሽና ትውኪያ እና ወዘተ

በሁለተኛው እርከን (Toxic Phase) ውስጥ የሚከተሉት ምልክቶችና የህመም ስሜቶች ይታያሉ፡-
- ከፍተኛ የሆነ ትኩሣትና የተለያዩ የውስጥ አካላት /ጉበት፣ ኩላሊት ወዘተ/ ብግነት ይደርስባቸዋል፣
- የሆድ ህመምና ትውኪያ
- የመድማት ችግር፡- ከአፍ፣ አፍንጫና ሆድ ዕቃ የመድማት ደም ማስታወክ እንዲሁም ደም ማስቀመጥ
- የአይን ቢጫ መሆን
- የሽንት መጠን መቀነስ፣ መቅላት እና የመሣሠሉት የሚታዩ ሲሆን አስፈላጊው አስቸኳይ የህክምና እርዳታ ካልተደረገ ከ10-14 ቀን ውስጥ ሊገድል ይችላል፡፡

5. ምርመራና ህክምና

ከላይ የተጠቀሱትን የበሽታ ስሜቶችና ምልክቶች የተሠማው ሰው ወዲያውኑ ፈጥኖ ወደ ጤና ድርጅት በመሄድ አስፈላጊውን የባለሙያ ምክርና ምርመራ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በቢጫ ወባ በሽታ የተያዘ ሰው ቶሎ ምርመራና የህክምና ዕርዳታ ካላገኘና ከዘገየ ለህልፈተ ህይወት ሊዳረግ ይችላል፡፡

6. የቢጫ ወባ በሽታ መከላከያ ዘዴዎች

የቢጫ ወባን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከምንጠቀምባቸው ዘዴዎች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. በሽታው በተከሰተባቸው አካባቢዎች በሚደረግ የክትባት ዘመቻ ህብረተሰቡ በንቃት መሣተፍ፣

2. በሽታ በተከሰተበት ወቅትና አካባቢ መንግስታዊ ድርጅቶችና ህዝባዊ ተቋማት ህብረተሰቡን በማንቀሣቀስ የትንኝ መራቢያ ቦታዎችን እንዲያፋስስና እንዲያደረቅ በማድረግ የአካባቢ ቁጥጥር ሥራን አጠናክሮ መስራት፣ ቤትን በፀረ ትንኝ ኬሚካል ማስረጨት፣

3. በአቅራቢያ ያሉ ጤና ድርጅቶች እና ጤና ጽ/ቤቶች ከሌሎች ማንግስታዊና ህዝባዊ ተቋሞችጋር በመተባበር በህብረተሰቡ ውስጥ የተጠናከረ አሠሣ ማድረግና ህብረተሰቡን ስለበሽታው ግንዛቤ ማስጨበጥ፣

4. ሪፖርት ማድረግ - በአንድ አካባቢ የቢጫ ወባ በሽታ መኖሩ ከተጠረጠረ በክልሉ ለሚገኙ መንግስታዊና ህዝባዊ ድርጅቶች እንደዚሁም በአቅራቢያው ላሉ ጤና ድርጅቶች ማሣወቅ፡፡